# ቆሬ ዓመፀ

## ዘኍልቍ ምዕራፍ 16 እና 17

**የልጆቻችሁን ፍላጎትና ስሜት ግምት ውስጥ በማስገባት መልመጃዎችን ምረጡ። መልመጃዎቹን በቤተሰብ ተወያዩባቸው።**



## ዘኍልቍ ምዕራፍ 16ን እና 17ን አንብቡ።

ቀጥሎም ሥዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አንብቡ (ኢንተርኔት ላይ እንዳላችሁ ወይም በወረቀት አትማችሁ ማንበብ ትችላላችሁ)፤ ከዚያም በታሪኩ መጨረሻ ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው።

**እንዲህ አድርጉ፦** *የይሖዋን ሥልጣን አክብሩ* (እንግሊዝኛ) የተባለውን ቪዲዮ ተመልከቱ። (በዲቪዲ ወይም www.jw.org/am ላይ የሕትመት ውጤቶች > ቪዲዮዎች በሚለው ሥር ይገኛል) ከዚያም እነዚህን ጥያቄዎች በቤተሰብ ተወያዩባቸው፦ (1) ቆሬ እና ተከታዮቹ ታማኝ ሳይሆኑ የቀሩት በየትኞቹ መንገዶች ነው? (2) የይሖዋን ሥልጣን እንደምናከብር ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው?

## ማተም የምትችላቸው ተጨማሪ መልመጃዎች



### የሥዕል ጨዋታ

**ቀለም የሚቀባ ሥዕል፦** ዘፀአት 28:15-21ን አንብቡ። ከዚያም ልጆቻችሁ በደረት ኪሱ ላይ የሚገኙትን የከበሩ ድንጋዮች ቀለም እንዲቀቡ አድርጉ። ሲጨርሱ የደረት ኪሱን ቆርጠው በማውጣት ደረታቸው ላይ እንዲያደርጉት እርዷቸው።



### ለጥናት የሚረዳ መልመጃ

**ፓዝል፦** ትንሹ ልጃችሁ ፓዝሉን እንዲቆራርጥና ገጣጥሞ የእስራኤላውያንን ሰፈር እንዲሠራ አድርጉ። ከዚያም የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮችን የሚያሳዩትን ሥዕሎች ቆርጦ ያውጣቸው። በአንደኛው ባዶ ምስል ላይ ስሙን እንዲጽፍና ራሱን እንዲሥል ጠይቁት። በመጨረሻም ልጆቻችሁ ተቆርጠው የወጡትን ባለታሪኮችና የተገጣጠመውን ፓዝል ተጠቅመው የቆሬን ታሪክ በድራማ መልክ እንዲሠሩ አድርጉ። በእያንዳንዱ ትዕይንት ላይ ልጃችሁን እንዲህ እያላችሁ ጠይቁት፦ “አንተ እዚያ ሆነህ ቢሆን ኖሮ ከማን ጎን ትቆም ነበር?”



### ካርድ በመሰብሰብ መማር

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ካርድ፦** በአጭሩ የቀረበውን የሕይወት ታሪክ አንብቡ። በካርዱ ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ልጆቻችሁን ጠይቋቸው። ልጆቻችሁ በዚህ ካርድና jw.org ላይ በወጡት ሌሎች ካርዶች ላይ የተጠቀሱ የሌዊ ነገድ አባል የሆኑ አምስት ሰዎችን ፈልገው እንዲያገኙ አድርጉ፦ (1) በልጅነቱ በማደሪያው ድንኳን ማገልገል የጀመረ ነቢይ፣ (2) የአንበረም ሦስት ልጆች እና (3) በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገኙ አራት መጽሐፍትን የጻፈ የካህን ልጅ።—**ፍንጭ፦** አንደኛ ሳሙኤል 3:1ን፣ 1 ዜና መዋዕል 6:1-3, 33, 34ን እና ኤርምያስ 1:1ን አንብቡ።

**መልስ፦** 1. ሳሙኤል 2. አሮን፣ ሙሴ፣ ሚርያም 3. ኤርምያስ

www.jw.org/am © 2014 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania